# የአደራ ቃል

በአላማ ጸንተው ፤ ባንድ የተሰለፉ
በከተማም በዱር ፤ ቀርተው የረገፉ
ለፍትህ ለርትዕ ፤ ተዋድቀው ያለፉ
ለወገናቸው ክብር ፤ ቀርተው ያንቀላፉ
ይነገር ገድላቸው ፤ መቼም አይረሱ
ትላንትናም ዛሬም ፤ አልሞተም መንፈሱ
ይንቦግቦግ እሳቱ ፤ ጭቁኑን ቀስቅሱ
ጸረ ህዝብ ይመታ ፤ ስርአቱን ገርስሱ
በህብረት አንድ ላይ ፤ ለአመፅ ተነሱ ።

ያደራ ቃላቸው ፤ ከመቃብር ሆኖ
ዛሬም ይጠራሃል ፤ ግባ ጫካ ፋኖ
መሳሪያውም ይውረድ ፤ ከተሰቀለበት
የወደቁት ጓዶች ፤ ቃል ኪዳን አለበት
በጨቋኝ ደም ይዋጅ ፤ የደም ዕዳ አለበት
ይከፈል  ዋጋቸው ፤ ወድቀን እንጣልበት ።

ዛሬም እንደ ጥንቱ ፤ በደም ባጥንታችን
ሞትን ለሞቱልን ፤ በቀድሞ ጓዳችን
ቃል ኪዳን አለብን ፤ ይከፈል እዳችን
አርማውን አንስተን ፤ ይቀጥል ትግላችን ።

ፍኖ ግባ ጫካ ፤ ሙታን ይጠሩሀል
ጫካው ተረተረሩ ፤ አሻግሮ ያይሀል
ከሳቱ ከቋያው  ፤  ግባ እንጂ ከመሀል
ላንተም ያልለመድከው ፤ መቼ ይመችሀል
ጥሎ መጣል እንደሁ፤  ወትሮም ያምርብሀል ።

ከታዛቢው

January 11/10